# ይድረስ በሲያትል ለምትኖሩ የኢትዮጵያ ልጆች

ውድ በሲያትል የምትኖሩ ያገሬ ልጆች ሆይ !እንደምን ከረማችሁ ?ለመሆኑ የክረምቱ ብርድ እንዴት እያደረጋችሁ ነው? አይዞአችሁ በዚህ ክረምት አንድ አጥንት ለጎናችሁ አድርጉና ብርዱን ለመቋቋም ሞክሩ።ለነገሩ የዚህ አገር ብርድ ገራ ገር በመሆኑ ማንንም ለክፍ ሳይሰጥ በመጠባት እግሩ መመለሱ አይቀርም።አንዳንዶቹ ደግሞ በዚህ ብርድ እያሳበቡ ጉዝጓዝ ጎዝጉዘው እጣን አጭሰው ቅምቀማና ቅምያ መያዛቸውን ሰምተናል። ይህን ነገር ለመቃወም የምትሞክሩ ካላቸው ደግሞ የአጼ መለስ ዜናዊ ሚስት አዜብን ኪሳራ ላይ ለመጣል የሚደረግ ደባ መሆኑን አሳውቁ  ባልፍ መልካም ሳይሆን አይቀረም።ወ/ሮ አዜብ የአገር ኸዚ ሚስት ቢሆኑም ጫት/የሚያደነዝዝ እጽ/ ለመነገድ/ለማስነገድ የሚከለክላቸው ምንም የሞራልም ሆነ የባህል ክልከላ የለባቸውም።ምንም ይሁን  የሲያትል ሰዎች የአዲስ አበባውን ንጉስ እንደማትፈሩ አሳይታችኋል እኮ።አቦ ይመቻችሁ።

የዚህን አገር ብርድ ሳወራ የኢትዮጵያችን የጥቅምት ወር ብርድ ትዝ ብሎኝ “በጥቅምት አንድ አጥንት” ብየ ልመክር ፈልጌ ተውኩት።እንኳን ለጥቅምት ብርድ አይደለም ለፋሲካ እንኳ ሰው አጥንት እየተዋዋሰ ጦሙን በሚፊታበት አገር ውስጥ ለብርድ ቅልጥም ቀቅላችሁ ሾርባውን ጠጡ  ብሎ መምከር እንደ ወያኔ የሰው ብሶት የማይሰማው ያሰኛል እንጂ የሚያስገኘው ትርፍ ስለሌለው ምክሬን ትቼዋለሁ።ታዲያ እንዲህ በከፋ ዘመን ድሮ ክረምት ሲገባ “በክረምት አንድ አጥንት” እየተባለ ይነገር ነበር ብለን እናልፈዋለን እንጂ አሁን አንጠቀምበትም።እረ ለመሆኑ ምንድ ነው አሁን አለን ብለን ያምናወራው ቁም ነገር ?ሁሉም ድሮ ቀረ እኮ።ሽምግልናውም ድሮ ቀረ።የተናገርኩት ከሚቀር የወልድኩት ይሙት የሚባል መሪ ቃል የትአባቱ እንደደረሰ ማንም ሊቅ መርምሮ አላገኘውም።አያቶቻችን ያሳዩን ጀግንነት የት ደረሰ ብለን ብንጠይቅ የሚነግረን አጥተናል።የሃይማኖት አባቶች ግርማ ሞገስም እንደ ጠዋት ጤዛ እርግፍ ብሎ ሲጠፋ ስናይ ከክረምቱ ብርድ ይልቅ የእነርሱ እንዲያ መሆን አመዳችንን ቡን አድርጎት ይኸው ገርጥተን ቀርተናል።የአገራችንን ሁኔታ ስናይ  የዓለም ፍጻሜ የቀረበ እስከሚመስለን ድረስ ተገርመንና አዝነን ቁጭ በለናል።

ሲያትሎች አይዞአችሁ ይህ ክረምት አይደለም ሰማይና ምድር ሳይቀሩ ያልፋሉ።እንደ ወረቀት ጥቅልል ብለው እያየናቸው ያልፋሉ።ያን ግዜ ብርድ የለ ወበቅ የለ።ገዢ የለ ተገዢ የለ።ወያኔ የለ ህወሃት የለ።መለስ የለ ባለሃውልቱ ፓትሪያሪክ የለ።ሁሉም እኩል ሁሉም አንድ።አንድ ዳኛ አንድ ፈጣሪ።አቤት እንዴት ጥሩ ነገር ነው እባካችሁ ?

እረ እናተየ ከሰሞኑ ተሰርቶ በብሄራዊ ሙዚየም እንዲቀመጥ ስለተወሰነው ሃውልት ሰምታችኋል ?ሃውልት ስል እኮ ትዝ ብሎኝ ነው።ይሄውላችሁ ሳሞራ የኑስ የሚባል አንድ ሰው አለ።ይሄኛው “ነበር” አይባልም “አለ” ነው የሚባለው።ሁሉም በነበር ሲቀር እነዚህ ሰዎች ብቻ  አሉ ይባላሉ።ታዲያ ሳሞራ ት/ቱን አስራ አንደኛ ክፍል ላይ ገትሮት ባቦጊዳ ላይ ሸፍቶ ከርሞ ሲያበቃ የመጀመሪያው ባለሙሉ ማእረግ ጄኔራል ተብሎ ሃውልት ተሰራለትና በብሄራዊ ሙዚየም እንዲቀመጥ ተደረገ።ይህ ሰው ለአማራ ሕዝብ ባለው ስር የሰደደ ጥላቻ የሚታወቅ መሆኑን በተለያየ አጋጣሚዎች ሰምተናል።የአማራ ስመ ጥር የጦር መኮንኖች በየእስር ቤቱ ዘር እንዳያፈሩ በብልቶቻቸው ላይ ብሎኬት እየተንጠለጠለ ሲሰቃዩና የኦሮሞዎቹ መኮንኖች አገራቸውን ጥለው እንዲሰደዱ ሲደረግ ይኸው ለሳሞራ ሃውልት ቆመለት።ኦሮሞውን ለማሳደድ አማራውን ለማዋረድ በርትቶ በመስራቱ ይሄው ለዚህ ማእረግ በቃ።ካሁን ወዲያ ለሳሞራ ከኢትዮጵያ ይልቅ የቆመለት ሃውልት ነው አገሩ።ለኢትዮጵያ ሳይሆን ለሃውልቱ ሲል ህይወቱን አሳልፎ እንዲሰጥ የሚያስገድደው ሁኔታ ውስጥ ገብቷል።ሚሊየኖች አልቀው የሳሞራ ሃውልት ብቻ በኢትዮጵያዊያኑ አጽም ላይ ቢቆም የሳሞራ ድልና ይህይወቱ ስኬት ነው።አቤት አገር።ሁል ግዜ የሚያስቡልሽና የሚሞቱልሽ የትም ተጥለው የሚያፈርሱሽና የሚገደሉሽ ብቻ የሚኖሩብሽ የምትገርሚ ጉደኛ አገር።

እረ ለመሆኑ መንግስቱ ነዋይ የት ነው ያለው ?በዚያ በንጉስ ወቀት ከራሱ ድሎትና ምቾት ይልቅ የዜጎቹን ብሶት በማየቱ መስዋእት ሁኖ ስለድሆች የተሰዋው ጀግና።እርሱ አይደለም እንዴ የሚከተለውን ቅኔ የተቀኘው?

ሞቼ እየተንሳሁ ለሙት እንደገና፤

አንድ ሞት ላገሬ አይበቃምና።

እንዲህ ያሉ ስመ ጥር ጀግኖች መተኪያ የሌለውን ህይወታቸውን ላገራቸው አሳልፈው የሰጡ የትም ተጥለውና አስታዋሽ አጥተው ይሄው ሳሞራን የመሰሉ ጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎች ሃውልት እየተሰራላቸው እንዲቆምላቸው ተደርጓል።

ጉድ በል አሊ በርኬ።ከሶማሌ ጋር አንገት ላገት ተናንቀህ ያገርህን ድንበር አስከብረህ ህዝብህን አኩርተህ ስታበቃ ለጎንህ ማረፊያ ሳይኖርህ ለምትንከራተተው ያገሬ ጀግና።ጉድ በሉ የኢትዮጵያ ውድ ልጆች በየሜዳው ወድቃችሁ የቀራችሁ።እናንተ ሁላችሁ በነበር ስትቀሩ ትላንት ድልድይ ሲያፈርሱ የነበሩ ዛሬ ሃውልት እየቆመላቸው ነው።ሳሞራ የኑስ ሆይ ዝም ብለህ ስም አጠራርህ

ሳይታወቅ ቢቀር ይሻልህ ነበር።ገና ከየትኛው ጠላት በየትኛው ግንባር ተዋግተህ አገርህን ከአደጋ እንደተከላከልክ የማስረዳት ሃላፊነት አለብህ።ለዚህ ሁኔታ ያበቃህ ምን እንደሆነ ማብራራት ይጠበቅብሃል።ካንተ ጋር ከነበሩት የጦር መኮንኖች መካከል ከስየ አብርሃ ወይም ደግሞ ከጻድቃን ወይም ደግሞ ከሃይሎም ዓርአያ በምን ተሽለህና ልቀህ ይህ ሃውልት በስምህ እንደቆመልህ መናገር አለብህ።እንዴትስ ሁኖ የመጀመሪያ ድግሪ ሳይኖርህ ማስትሬት ድግሪ እንደጨበጥክ ልናውቅ እንፈልጋለንና ከቻልክ ጻፍ ካልቻልክ አጽፍና እንይ።

ከሳሞራ ሃውልት ስር ከውጭ አገር ማስትሬት ድግሪ አግኝቷል የሚል ማስታወሻ ይነበባል።11ኛ እና 12ኛ ክፍልን እንዲሁም የመጀመሪያ ዲግሪውን የት እንዳገኘ ብርቱ ሚስጥር ተብሎ ዝም ተብሏል።አሁን ከዚህ በላይ ምን ሙስና በዝህ ምድር ላይ ይኖራል ብለን የምንጠይቀውም አካል ስለሌለ ለግዜው ዝም ብለናል። ይህ ነገር በጸረ ሙስና ኮሚሽን ተመረምሮ እንዲገለጽልን ብንጠይቅም ጸረ ሙስና ኮሚሽን አፋን አሹሎ አይሰማም ብሎአል።ወደ ፊት ግን ከ11ኛ ክፍል ተነስቶ ከውጭ አገር ማስትሬት ዲግሪ መጫን እንዴት እንደሚቻል ለትውልዱ ሁሉ ይገለጻል።እውነቱን ተናግሮ ከመሸበት ከማደር ይልቅ ዋሽቶና አጨበርብሮ ምንም ጥቅም የሌለው ማስትሬት ድግሪ መጫን የተከበረበት አገር መሆኑንም እንማራለን።ይህም አንድ ትምህርት ነው።ከወያኔ ባለስልጣናት ኢትዮጵያዊያን የሚማሩት ይህንን የመሰሉ የአገራችንን ወግና ባህል የሚያዋርዱ ተግባራትን ነው።አዎን አሁን በወያኔ ዘመን "ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል" የሚለው ተረት የአገሪቷ መሪ ሃሳብ ሆነ።

የሆኖ ሆኖ ከ11ኛ ክፍል ተነስቶ ማስትሬት ድግሪ ለጫነ ለዚህ ሰው ቋሚ ምስክር የሚሆን ሃውልት ቢሰራለት ምን አለበት የሚሉ ሰዎችን ጸጥ ብለን ሰምተናቸዋል።አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ሳሞራ የኑስ ካርታ ይዞ የቆመበትን ቦታ ለማሳየት መከራውን ሲያይ የሚውል ተጋዳላይ ነው ብለው አምተው አምተው እንደኩፍኝ ከወጣላቸው በኋላ ሃውልቱ መታነጹን ሲያዩ አሁን የዘመን ፍጻሜ ቀረበ ብለው ዝም ብለዋል።ሌሎች ለዚያች ባንዲራና ለዚያች አገር ህይወታቸውን አሳልፈው የሰጡ ድንቅ ኢትዮጵያዊያን በነበር ቀሩና ይሄው ሳሞራ የኑስ የመጀመሪያው ባለሙሉ ማእረግ ጀኔራል ተብሎ ሃውልት ቆመለት።እኔን የሚገርመኝ እነ አጤ መለስ ዜናዊ አድሜ ልካቸውን ያችን አገር ለመግዛት ህልም ኑሮአቸው ነው እንዲህ እዚያና እዚህ በጣም ለሚጠሉ ሰዎች ሃውልት የሚያቆሙላቸው?ብሄራዊ ሙዝየማችን ግን የማንም ዘረኛና ዘራፊ ስርዓት አገልጋይ ግለሰብ ሃውልት ተሽክሞ አይኖርም።

ለነገሩ እነርሱ ምን ያድርጉ ከወዲህ ሰው ሲታጣ።

እረ ሲያትሎች አጤ መለስ ዜናዊ ውጭ አገር ሲሄዱ ፈገግታ ከየት ነው የሚመጣላቸው ?ሰሞኑን ወደ ኮሪያ ገስግሰው ሂደው ነበር።አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት እርሳቸው በልመና የሚሰተካከላቸው ሰለሌለ አፍሪካን ወክለው እንዲለምኑ ነው የተላኩት ይላሉ።ለማንኛውም የሃብታም አገራት መሪዎች ስብሰባ አለ የተባለበት ቦታ አጤ መለስ ዜናዊ ይገኙና አስር ሚሊዮን ስጡኝ ሃያ ሚሊዮን ካልሰጣችሁ ሞቼ እገኛለሁ እንዲያውም መቶ ሚሊዮን ካልሰጣችሁ ክልሉ የጦርነት ቀጠና ይሆናል እያሉ እጅ እየነሱ ይማጸናሉ።እንደው ልመና የማይታክታቸው የሰው ዓይን የማያስፈራቸው ብርቱ ታጋይ እርሳቸውን አየው። በነገራችን ላይ ልመና በእኛ አገር ነውር ተግባር አይደለም እንዴ ?ወይስ የአጤ መለስ ዜናዊ የእርዳታ ያለህ እያሉ በየአገሩ እየዞሩ ደጅ መጥናት ልመና አይባልም ? ሁሉም የአፍሪካ መሪዎች የማንንም ደጅ አንጠናም የሰውንም ፊት አናይም ብለው ህዝባቸውንና የየአገራቸውን ነጋዲያንንና ምሁራንን አስተባበረው ለልማት ሲራወጡ አጤ መለስ ግን ህዝባቸውን ለስደትና ለእስር ዳርገው በየአገራቱ ለልመና ሲሯሯጡ ይውላሉ።አሳፋሪ።

ከልመናው በኋላ ፎቶ የማይቀር ነው።

አጤ መለስ ከልመናው በተጨማሪ የተካኑበት ቁም ነገር ቢኖር ፎቶ መነሳት ነው። ሰውየው ሲያደቡ ውለው ስብሰባው እንዳለቀ ተሯሩጠው ከባራክ ኦባማ ጎን መቆም ባይሆንላቸው እንደምንም ብለው ከታላቁ መሪ ጀርባ አንገታቸውን ብቅ አድርገው ቁመው ፈገግታ በፈገግታ ሆነው ፎቶ ይነሳሉ።እኔን ግራ ግብት ያለኝ ነገር ግን ይህ ፈገግታ ከየት አባቱ እንደሚመጣ አለማወቄ ነው።ፈገግታቸውን ትኩር ብየ ስመለከተው ግን ሁለት ነገሮችን የሚናገር ይመስላል። አንደኛው "እናንተ ዲያስፖራ አክራሪዎች ይሄውላችሁ እንዲህ የታውኩ ነኝ።እኔን መገልበጥ የሚሞከር አይደለም ከማን ጋር እንደምውል እዩ" የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ "ስማ ባራክ ኦባማ ካንተ በሃብትም ሆነ በማንኛውም ነገር እንደማላንስ እንድታውቀው" የሚል ይመስላል።ለነገሩ አጤው እኮ የገንዘባቸው መጠን ባራክ ኦባማ ካላቸው እንደሚበልጥ ከሰማን ቆይተናል።እኔ የምለው ግን አጤ መለስ ዜናዊ ባገር ቤት ውስጥ ፎቶ ሲነሱ ለምንድ ነው ያን ፈገግታ የማያሳዩት ?ለምን እንዲህ ጨቦ እንደሚሰሩብን እንድየ ብቻ ነው የሚያውቀው።አገራችንን ወስደው እኛን አገር አልባ አደረጉን።አሁን ደግሞ ፈገግታ ለእናንተ አይገባችሁም ብለው ለኮሪያውያን ሲስቁ ይውላሉ።ለነገሩ ፍቅር ከሌለው ደረቅ ፈገግታ አባ ጨጓሬ የመሰለ ፊታቸውን ማየቱ ሳይሻል ይቀራል ?

ሲያትሎች ባለፈው አንድ ግሩም ነገር እንደጀመራችሁ ሰማን።"የአንድነትና የትብብር ፎረም"ለመፍጠር እየሞከራችሁ እንደሆነ። እንዴት ግሩም ነገር መሰላችሁ።በርቱ በርቱ እደጉ ተመንደጉ።አሁን ነቄ ብላችኋል።እኛ እዚህ አማራ ኦሮሞ ኦጋዴን ሌላም

ሌላም እያልን ስንከፋፈል ወያኔ ያማራውን ቅስም ሰበርኩ እያለ ይፎክራል።ኦሮሞውን ረግጬ በቁጥጥሬ ስር አስገብቼአለሁ እያለ ይለፍፋል።ኦጋዴኑን ብትንትኑን አውጥቼአለሁ እያለ ያቅራራል።ሌሎችን ደግሞ ምንም የማያውቁ የእግዜር በጎች ስለሆኑ “Harmless” ናቸው ብሎ ትቶአቸዋል።እንግዲህ እንዲህ ያለውን ዘረኛ አገዛዝ ለማቆምና ለሁላችንም የምትሆን አገር ለመፍጠር አንድ ላይ ከመቆም በቀር ሌላ ምንም የቀረን አማራጭ የለንም።እናንተም ይህን ነገር ተገንዝባችሁ አንድ ላይ ለመቆም ተቀራርባችሁ ምክክር መጀመራችሁ በራሱ አንድ በጎ ነገር ነውና በርቱ በርቱ እንላለን።አዎን ሰው በህይወት አለ የሚባለው ከራሱ በላይ አንድ የሚኖርለት ነገር ሲኖር ነው።ሁላችንም ነገ እንሞታለን ይህን በማወቃችን ደግሞ ከሌሎች እንስሶች እንለያለን።ነገ የምንሞት ከሆነ ደግሞ ዛሬ የምንኖርለት አንድ ከራሳችን በላይ የሆነ ነገር ሊኖረን ይገባል ማለት ነው።እርሱም ኢትዮጵያችን እንደ አገር ተሥርታ አልቃና ሁላችንም እኩል ሁነን ያለምንም ፍርሃትና ሰቆቃ የምንኖርባት ነጻ አገር ሁና ማየት መሆን አለበት።

ይሄውላችሁ እንግዲህ አሁን ነው

“ፉኖ ተሠማራ

እንደ ሆቺ ሚኒ እንደ ቼ ጉቬራ።”

እያልን ከየቦታው የኢትዮጵያ ልጆች መሳበሰብ ያለብን።

አገር የሌለው ሰው ዝም ብሎ አይተኛም።አገራችሁ የወረብሎችና የዘረኞች መጫወቻ ሁናለች።እናንተ በዚህ የታሪክ አጋጣሚ የተገኛችሁ ትውልዶች ናችሁ ይህ ማለት ኃላፊነት አለባችሁ ማለት ነው።አሁን እንደ ኢትዮጵያዊ የምታስቡበት ግዜ ደርሷል።ኢትዮጵያዊ የሚያስበው ከራሱ በላይ ልቆ ላለ ትልቅ ቁም ነገር ነው።ኢትዮጵያዊ ከሚበላው ቁርጥ ሥጋና ከሚጠጣው ወይን ጠጅ ይልቅ የሚኖርለት የፍትህ የነጻነት የህግ የበላይነትን የመሳሰሉ ታላልቅ ቁም ነገሮች አሉት።ኢትዮጵያዊ ማለት የተናገርኩት ከሚቀር የወለድኩት ይሙት ብሎ ስለ እውነት ጸንቶ የሚቆም ነው።ኢትዮጵያዊ ማለት ለሰው ልጆች ሰብአዊ መብት የሚታገል ነው።ኢትዮጵያዊ ማለት እምቢ ለአገሬ የሚል ነው።ኢትዮጵያዊ ማለት ውረደትን በጸጋ የሚቀበል ሳይሆን ለተዋረዱት መከታ የሚሆን ማለት ነው።ኢትዮጵያዊ እኔ ከሞትኩ ስርዶ አይበቀል አይልም።እንዲህ የሚል ህ.ወ.ሃ.ት ብቻ ነው።እኛ ኢትዮጵያዊያን እንዲህ የሚል ተረት አለን እንጂ በተግባር እንዲያ አይደለንም።ተረቱን ግን የምር ወስደው በተግባር ምን እንደሚመስል ያሳዩን ወያኔዎች ናቸው።ይህ ማብቃት አለበት።

ሲያትሎች ጅምራችሁ ጥሩ ነው።ከሚለያያችሁ ነገር ይልቅ አንድ የሚያደርጋችሁ በርካታ ቁም ነገሮች አሉ።በእነዚያ ላይ ብቻ አትኩራችሁ ትብብራችሁን ልታጎለብቱ ይገባል።ለሌሎችም ጥሩ ዓርዓያና ምሳሌ ትሆናላችሁ የሚል ጽኑ እምነት አለን።እኛም ከጎናችሁ ነን ብለን ወደ ሌላ ጨዋታ እንገባለን።

ይሄውላችሁ ከሰሞኑ ኢትዮጵያችን ውስጥ የኑሮው ንረት ህዝባችን ከሚችለው በላይ አሻቅቧል። የስኳር ዋጋም የሚቀመስ አይደለም።ስኳር ቀምሶ የማያውቀው ያገራችን ገበሬ ስኳር ስለቀመሰ ነው ብለው ውሸት የማያውቁት አጤ መለስ ዜናዊ ስለተናገሩ ጉዳዩን ይሁን ብለነው ነበር።ያልታደለው ያገራችን ገበሬ ስኳርን ከሚቀመስ እንደ ድሮው ማር እየበላ ስኳሩን ለከተሜው ቢተውለት ምናለ እያልን ስንመኝ ከረምን።ገበሬው ግን ቀፎ የሚሰቅልበት ዝግባና ዋርካ ሁሉ በወያኔዎች ተመንጥሮ ስላለቀ ማር ማምረቱን ትቷል።በዚህም ስኳር መቅመሱን አላቆም ብሎ የስኳሩን ዋጋ እንዲሰቀል አድርጎታል።የንጉስ መለስ ዜናዊ የኢኮኖሚ እድገት ስኬት ይሄው በልቶ የሚያድረውን ህዝብ እየቀመሰ እንዲኖር ማደረጉ ነው።

ምን ያልጨመረ ነገር አለ ?አንድ ሊትር ዘይት ሰላሳ የኢትዮጵያ ብር ላይ ደርሶ አልወርድም ብሎአል።አንዳንድ ወግ አጥባቂ ክርስትያኖች ይሄ ሰላሳ ብር ነገር አለው ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ የሸጠበት ዋጋ በመሆኑ 29.99 ካልሆነም 30.01 አርጉት ቢባሉ ባለሃብቶቹ በጄ አላሉም።ምነው ቢባሉ የባሰ እንዳይመጣ ዝም ብትሉ ይሻላል  አሉ ይባላል።

እረ ምን ያልጨመረ ነገር አለ ?አንድ የማውቀው ሰው እንደነገረኝ የሴተኛ አዳሪ “የሸሌዎች” ዋጋም ጨምሮአል አሉ።እነርሱ ደግሞ እያሽሟጠጡ ነዳጅ ጨምሮ የለ እንዴ እያሉ በወንደ-ላጤው ላይ ይላጡበታል።ላንድ ሌሊት ሃምሳ ብር የነበረው ዛሬ ድፍን ሁለት መቶ ብር ሲጠይቁ ከእንትኑ በኋላ ድግሪ ወይም ዲፕሎማ የሚሰጡ ነው የሚመስሉት።ደግሞ አንተ ባትከፍለኝ ፊሊፒኖና ቻይና ቆሞ ይሂድ ሶስትና አራት መቶ ብር ይከፍላል እያሉ በሃበሻው ላጤ ላይ ያላግጣሉ አሉ።እኔማ እሰይ ደግ አደረጉ አልኩ።ላንድም አበሻ በጄ እንዳትሉ ብየ ገና እመክራቸዋለሁ።እናንተ ሴተኛ አዳሪዎች ሆይ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ኮርስ ወስዳችሁ ልማታዊ ሸሌ እንድትሆኑ መንግስት ፍላጎቱ ነውና አስቡበት።ይህች ፊሊፒኖና ቻይና ባገራችን ያፈራችውን ገንዘብ ቋጥራ አገሯ እንዳትገባ በርትታችሁ ሳትሰለቹ ስሩ።

ፊሊፕኖ ከየት መጣ ለምትሉ ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ የጉልበት ስራ የሚሰራ ስለጠፋ ወደ አምስት ሺህ የሚጠጉ ፊሊፒኖዎች አዲስ አበባ ውስጥ በሼኩ አማካኝነት ገብተዋል።ገቡ ከማለት ግን ዘነቡ ማለት ሳይገልጸው አይቀርም።ዘንበው ዘንበው

ይህን ድሃ ህዝብ የቻሉትን ያህል እያረሰረሱት ነው።አሁን በቅርቡ አባቱ ቻይና ወይም ደግሞ ፊልፒኖ የሆኑ ህጻናት ውር ውር ሲሉ አይተን እንዴ ይህ አገር የማን ነው ብለን ግራ እንዳንጋባ ካሁኑ እራሳችንን ብናዘጋጅ መልካም ነው።እረ ለመሆኑ እንዲህ ያሉ ልጆች የኢትዮጵያን ዜግነት የሚያገኙት በምን ህግ ነው ?አገሪቷ እኮ የዜግነት ህግ የላትም።ለነገሩ የአገሪቷ ህግ በሙሉ የአጤ መለስ ስሜት ስለሆነ ስለ ህግ አትጨነቁ።ተውት እኔም ትቼዋለሁ።

ዋጋቸው ከናሩ ነገሮች መካከል አንዱ ጋዜጣ ነው።የአንድ ጋዜጣ ዋጋ ድፍን ስድስት የኢትዮጵያ ብር።እግዚኦ በሉ ያገሬ ሰዎች።ድሮ በስድስት የኢትዮጵያ ብር አንድ ጥሩ ጠቦት ገዝታችሁ ከቤተሰቦቻችሁ ጋር ቀይ ወጥ አልጫ ወጥ ቅቅል እንዲሁም ጎመን በስጋ እያልን ስብራታችንን እንጠግን ነበር እኮ ብላችሁ የነገራችሁን ሰዎች ዛሬም በህይወት አላችሁ።አይኖቻችሁ እንዲህ ድንቅ ነገር በማየታቸው የተከበሩ ናቸው።አዎን ይኸም ድሮ  ቀረ።አይ ልማት ያመጣው ጣጣ ሁሉንም ደግ ነገር እኮ በነበር አስቀረው።

አንድ በቅርበት የማውቀውና የንባብ ልክፍት ያለበት ሰው ጋዜጣ መግዛት ስላልቻልኩ ለወያኔ ሰላይ ለመሆን ተቀጠርኩ አለኝ።የሚሰልለውም ጋዜጦች ላይ የሚወጡትን ጽሁፎች በመከታተልና አደገኞችን እየለቀመ ለሚመለከተው ክፍል ማቅረብ ነው።ይህ የማውቀው ሰው ግን ወያኔን በእጅጉ የሚጠላ ነው።የወያኔ ሰላይ ባይሆን ኑሮ ጋዜጦቹን የት አግኝቶ ያነባቸው ነበር ?ስራስ ማን ይሰጠው ነበር ?እረ እንኳንም ሆንክ ወዳጄ ብየዋለሁ።እርሱ እዚያ ባይሆን ኑሮ አንዳንድ ወሬዎችን ከየት አገኝ ነበር ?የቀድሞ ጓደኞቻችንም እርሱን እየተከተሉ ያገኙትን ጋዜጣ ሁሉ በነጻ ይከሰክሱታል መባልን ሰምቼ የቤተሰቦቻችንን የታክስ ገንዘብ ተጫወታችሁበት ብየ ብቆጣቸው ስቀው ስቀው አላቆም ስላሉኝ ስልኬን ጥርቅም አደረኩት።የታክስ ገንዘባችን እንዲህ መቀለጃ ሲሆን ከማልቀስ ፋንታ በመሳቃቸው ገረመኝ።እረ ጥርሳቸውን በሙሉ  ምን  ያርገው  ?  ምንም።

እስኪ አንድ ነገር እንጨምር።ሰሞኑኑ ብሄረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ የልደት በዓሉን ያከብራል ሲባል ሰምታችሁ ይሆናል።የአማራውን ቅስም ለመስበር ወያኔዎች ጠፍጥፈው የሰሩት ድርጅት ነው።ድርጅቱንም የሚመሩት አማሮች ሳይሆኑ ሌሎች ናቸው።የዚህን ድርጅት የልደት በዓል ለማክበር ከአማራ ክልል መንግስት ካዝና  ከሃምሳ ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ተደርጓል።ያልተወለደ ጭንጋፍ ድርጅት እንዲህ የህዝቡን ገንዘብ ሲበላው ስናይ ጉድ በል ሸዋ ጉድ በል ጎንደር ጉድ በል ጎጃም ጉድ በል ወሎ ጉድ በይ ኢትዮጵያ ልጆችሽ ከቆሻሻ ገንዳ ውስጥ እየለቀሙ ሲመገቡ እነዚህ ሃምሳ ሚሊዮን ብር አውጥተው አስረሽ ምቺው እያሉ ነው።ትላንትና ደርግ በአገሪቷ ርእሰ ከተማ ላይ ቤት ሠራ ብለው የአዞ እንባ ሲያነቡ የከረሙ ሰዎች ዛሬ ከአስራ ሶስት ሚሊዮን በላይ ህዝብ የእለት ጉርስ ለማገኘት ልመና ላይ ተሰማርቶ እያለ ከሃምሳ ሚሊዮን ብር በላይ አውጥቶ ድግስ መደገስ ማለት ወያኔዎች ምን ያክል ለህዝባቸው  ሃዘኔታ ለአገራቸውም  ፍቅር እንደሌላቸው የሚያመለክት ነገር ነው።ይሄው እንዲህ እያልን ሃያ ዓመት  ሞላው።

ሰላም እንሁን።

ሰውለሰው ነኝ።